ዶናልድ ዋልሽ

# መጽሐፈ ፍልስፍና
## ሥጋዊ ወመንፈሳዊ



ትርጉም የኪዳ እንዳርጌ ዓለሙ

# መጽሐፈ-ፍልስፍና
## ሥጋዊ ወመንፈሳዊ

አስደማሚው ቃለ-ምልልስ

ቅጽ 1

ዶናልድ ዋልሽ

ትርጉም - በግዛው ያለው

# መግቢያ

- አስደማሚው ቃለ ምልልስ የተደረገው በቀጥታ ከ"አምላክ" ጋር ነው። እንዴት? መጽሐፉ መልስ አለው።

- ይህ መጽሐፍ የፍልስፍና፣ የሣይንስ፣ የሣይኮሎጂ፣ የስነ-መለኮት፣ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ ሣይንስ ወዘተ... መጽሐፍ ነው። የሠው ልጆች "*ዘመን መቆጠር ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ*" እስከ አሁኗ ቅጽበት ድረስ በየዕለቱ የምናነሣቸው ጥያቄዎች የተዳሠሡበት ነው።

- የዚህ መጽሃፍ አቀራረብም ሆነ ለጥያቄዎቹ የተሠጡት መልሶች በአብዛኛው ለየት ያሉ፣ ካላሰብነው አተያይ፣ እጅግ በጣም ጠለቅ ካለ አረዳድ ተቃኝተው የቀረቡ ናቸው። ጥያቄ አቅራቢው ፀሃፊው ዶናልድ ዋልሽ ሲሆን መላሹ ደግሞ "*አምላክ*" ነው። ዶናልድ ዋልሽ ላቀረባቸው ጥያቄዎች "*አምላክ*" የሠጣቸው መልሶች የነከረንን ግንዛቤ የሚገለባብጥ ነው። እምነታችንንና እውቀታችንን የሚሞግቱ ምክንያታዊና ሳይንሳዊ ምላሾችንም እናገኛለን። "*እንደዚህ አይነት መልስ ከሰው ጭንቅላት ሊፈልቅ ይችላል? ከእርሱ ካልሆነ በስተቀር*" ልንልም እንችላለን።

ይህንን መጽሀፍ ለመተርጎም ያነሣሣኝ ዋናው ነገር በመጽሃፉ ውስጥ የሠፈረው ቁም ነገርና፣ ከስሜታዊነትና ጭፍን አመለካከት ተላቀን ጠያቂና ምክንያታዊ እንድንሆን የሚያነቃቃን አቀራረቡ እንደመሆኑ መጠን አጽዕኖት የሠጠሁት ከቋንቋ (ቃላት) ይልቅ ዋና ቁም ነገሩን ወይም ጭብጡን ለአንባቢያን ከማድረሱ ላይ ነው። በመሆኑም አንዳንድ የሣይንስና የፍልስፍና ቃላትን አንዳንዴ የተሻለ ነው ባልኩት ቃል፣ አልፎ አልፎ ደግሞ (የራሴ ትርጉም አልዋጥልህ ሲለኝ) አንባቢው የራሱን ትርጓሜ በመተካት የበለጠ መረዳት እንዲችል የእንግሊዝኛውን ቃል ጎን ለጎን በማስቀመጥ ነው የተረጎምኩት።

የመጽሃፍ ርዕስ በእንግለዝኛው "Conversations with God"- *uncommon dialogue* የሚል ሲሆን ይህንን በቀጥታ

በመተርጎም ርዕስ ባደርገው እንባቢው ርዕሱን ብቻ በማየት ሙሉ በሙሉ ሃይማኖት ነክ መጽሃፍ ነው የሚል የተሳሳተ ግንዛቤን ሊይዝና ማስተላለፍ የተፈለገው ቁም ነገር ላይደርሰው ሊቀር ነው:: መጽሃፉ ደግሞ ሃይማኖታዊ ተልዕኮ የለውም:: ለመጽሀፉ ርዕስ እጩ የሚሆነው "መጽሐፌ ጨዋታ ሥጋዊ ወመንፈሳዊ" የሚለው ነበር (አለቃ ዘነበ ከጊዜ ቀደሙ እንጂ)

የሆነው ሆኖ በስተመጨረሻ ከአለቃ ዘነበ ጋር መጽሐፍ ጋር ተቀራራቢነት ቢኖረውም ሌላ ምርጫ ጠፋና መጽሐፈ-ፍልስፍና ሥጋዊ ወመንፈሳዊ የሚለው ርዕስ ተመርጦ ይሄው ተደርጓል::

ውድ አንባቢያን

ምንም ሆነ ምን መጽሃፉን በከፊል በማንበብ በችኮላ ፍርድ እንዳንሠጥ በፈጣሪ ስም አደራ እላለሁ:: እንደ እኔ እንደኔ ከፍልስፍና ነክ (metaphtsical) ትንታኔዎቹ ይልቅ በጣም የመሰጠኝና እንድተረጉመው ያነሳሳኝ በኑሮ ወይም በህይወት ዙሪያ የቀረቡት (existential) ትንታኔዎቹ ስለሆኑ አንባቢም ለዚያ ትኩረት ቢሰጥ እመርጣለሁ:: ከምንም በላይ ደግሞ እንግሊዝኛውን አግኝታችሁ ብታነቡት ምናልባት እኔ የፈጠርኩትን ክፍተት ሊደፍንላችሁ እንደሚችል አልጠራጠርም::

በተረፈ ግልጽ ያልሆነ ነገር ካለ ምናልባትም የእኔ የተርጓሚው ስህተት ሊሆን እንደሚችል ከወዲሁ እየጠቆምኩ፤ አንባብያን አስተያየታቸውን ወይም ከአተረጓጎም ጋር የተያያዙ ጥያቄዎቻችውን negashgo@gmail.com ቢልኩልኝ ምስጋናዬ በፈጣሪ ስም ታላቅ ነው::

መልካም ምንባብ!

ግዛው ያለው ነጋሽ

ግንቦት 2002 ዓ.ም

የምታነቡትን መረጃ አድምጡ። በቀጣይ የምትመለከቱትን ፊልም ታሪክ፣ ቀጥሎ የምታገኙት ሠው ሊያወራላችሁ የሚችለውን ነገር ወይም ደግሞ የቀጣዩን ወንዝ ወይም ውቅያኖስ ሹክሹክታ፤ ጆሮአችሁን የሚጠስቀውን ቀጣዩን ነፋስ አድምጡ። እነዚህ መሣሪያዎች በሙሉ የእኔ ናቸው። እነዚህ ጉዳናዎች በሙሉ ለእኔ ክፍት ናቸው። የምታዳምጡ ከሆን እነግራችኋለሁ። ከጋበዛችሁኝ ወደ እናንተ እመጣለሁ፣ እናም ሁሌም በእዚያ እንዳለሁ አሣያችኋለሁ። በሁሉም (መንገድ)

# 2

**የሕይወትን መንገድ ለማሳየኸኝ**
**ከፊትህ ጋር ደስታን አጠገብኸኝ፤**
**በቀኝህም የዘላለም ፍሥሃ አለ”**
**መዝሙር 16፡11**

Q፩ **ህይወቴን በሙሉ ወደ አምላክ የሚወስደውን መንገድ እፈልግ ነበር**

• እውቃለሁ ትፈልጉ ነበር።

Q፪ **እናም አሁን አገኘሁት። ነገር ግን አላመንኩትም። ልክ እዚህ ቁጭ ብዬ ይህንን ለራሴ እንደምጽፍ አይነት ነው የሚሠማኝ።**

• አዎ እንደዚያ እያደረግህ ነው።

Q፫ **ነገር ግን ይህ ከአምላክ ጋር እንደሚደረግ ግንኙነት አይነት ስሜት የለውም።**

እሀ ደውሎች እና ፊሽካዎች ፈልገህ ነው? እስቲ እንደዚያ ማድረግ የሚቻል እንደሆነ እያለሁ።

Q፬ **“ይህ መጽሐፍ በሙሉ አምላክን የሚሠድብ ነው” ብለው የሚያስቡ ሠዎች እንደሚኖሩ አታውቅም? ታውቃለህ። በተለይ ልክ እንደ ጥዉፍ ሠው አይነት ንግግር ከሆነ የባሠ ነው የሚሆነው።**

አንድ ነገር ልግለጽላችሁ — “አምላክ ራሱን የሚገልፀው በአንድ መንገድ ብቻ ነው” የሚል አመለካከት አላችሁ። ይህ በጣም አደገኛ አስተሳሰብ ነው። ይህ አስተሳሰብ አምላክን በየቦታው እንዳታዩ የሚገድብ ነው። አምላክ አንድ የሆነ ነገር ነው የሚመስለው ወይም የራሱ የሆነ ድምጽ ወይም መንገድ አለው ብላችሁ የምታስቡ ከሆነ ነጋ ጠባ ማታገኙኝ ነው የምታልፉት። እድሜ ልካችሁን አምላክን ስትፈልጉት ትኖራላችሁ ግን አታገኙትም። ምክንያቱም የምትፈልጉት ወንዱን ነው (ይህንን እንደምግባ ነው የተጠቀምኩበት)። አምላክን በጥልቅና በቅድስና ካላያችሁት የታላቁን ግማሽ ክፍል አጥታችሁታል ተብሏል። ያ ትልቅ እውነት ነው።

አምላክ በመፍራውና በጣፋጩ ነገር ሁሉ ያለ ደስታና ሐዘን ነው። ለእያንዳንዱ ነገር በስተጀርባ መልክታዊ አስማ አለ። ስለሆነም በሁሉም ነገር ያለው ነገር ሁሉ መልክተኛ ነው።

አሁን ለእያንዳንዳችሁ እየመራሁ ነው፡፡ እያንዳንዳችሁ ማን እንደሆናችሁ አውቃለሁ፡፡ መንገዳችሁን በእዚህ ቃላት ውስጥ የሚያገኙት የትኞቹ እንደሆኑ አውቃለሁ፡፡ (በሌሎቹ የመገናኛ መንገዶቼ እንደሚስተዋለው ሁሉ) ለእናንተም ጥቂቶቹ እንደሚሰሙ፣ ጥቂቶቹ ደግሞ ቢሰሙም ቅሉ ምንም እንደማያዳምጡ አውቃለሁ፡፡

Q17 መልካም፡፡ ይህ ደግሞ ሌላ ነገር ይዞ መጣ፡፡ አሁን እየገፋሁ ባለሁበት ቅጽበት ይህንን መጽሃፍ እንደማሣትመው እያሠብኩ ነው፡፡

አዎ፡፡ እና ይሄ ምን ችግር አለው?

Q18 "ይህንን የፃፈው ለገንዘብ ሲል ነው" የሚል ሙግት አያስነሣም? ይህ ነገር ታዲያ ሁሉንም ነገር ጥርጣሬ ላይ አይጥልም?

አንድ ነገር ለመፃፍ የምትነሣሣው ብዙ ገንዘብ ስለሚያስገኝልህ ነው?

Q19 አይደለም፡፡ ይህንን መጻፍ የጀመርኩት ለዚያ ብዬ አይደለም፡፡ እዕምሮዬ ላለፉት ሰላሳ ዓመታት ያህል በጥያቄዎች ተወጥሮ ስለነበር ነው፡፡ መልሳቸውን የተራብኩባቸው ጥያቄዎች ናቸው፡፡ ይህንን ጽሁፍ በመጽሃፍ መልክ የማሣተሙ ሀሣብ የመጣልኝ በኋላ ነው፡፡

ሃሳቡ ከእኔ ነው የመጣልህ፡፡

Q20 ከአንተ?

አዎ፡፡ እነዚህን ድንቅ ጥያቄዎችና መልሶቻቸውን ስታባክናቸው ዝም ብዬ የማይህ ይመስልሃል?

Q21 ይህንን አስቤው አላውቅም፡፡ ከጅምሩ ጥያቄዎች እንዲመለሱልኝ፣ ጭንቀቴ እንዲያበቃ፣ ፍለጋዬም እንዲቋጭ ነው ፍላጎቴ፡፡

ጥሩ፡፡ ስለዚህ "ምንድነው ያነሣሣኝ" ብለህ ማብሠልሰልህን አቁም! (አስሬ ደጋግመህ ይህንን ታብሰለስላለህ) እናም በጀመርነው እንቀጥል፦

በምናባችሁ ከሳላችሁት እጅግ የተሻለ ህይወት ጋር ህብረት የሌለው (የማይጣጣም) አንዳች ነገር ከተናገራችሁ፣ ሁለተኛ ያንን ቃል ላለመድገም በማስታወሻ ከትባችሁ አስቀምጡት። ከምርጡ እሣባችሁ ጋር የማይጣጣም አንዳች ነገር ካደረጋችሁ ያንን ድርጊት ሁለተኛ እንደማትደግሙት ወዲያውኑ ወስኑ። በዚህ ትልማችሁ ውስጥ የምታሳትፏቸውን ነገሮችን ሁሉ አስተካክሉ።

> ስለዚህ ጉዳይ ካሁን ቀደም ሰምቼ አውቃለሁ። ነገር ግን የማይታመን ነገር ሆኖ ስለሚታየኝ ሁሌም እቃወማለሁ። *"ታመህ የአልጋ ቁራኛ ብትሆንም መታመምህን መቀበል አይኖርብህም፣ ቤሳቤስቲን የሌለው መናጢ ደሃ ብትሆንም ደሃነኝ ማለት አይኖርብህም ። በንዴት ብትጦዝም ንዴትህን ማሣየት አይኖርብህም"* ይላሉ። ነገሩ እንዲያውም ሲኦል ስለገቡ ሦስቱ ሠዎች ቀልድ ያስታውሰኛል። አንዱ ካቶሊክ ነው። ሁለተኛው አይሁድ ሲሆን ሶስተኛው ደግሞ የዘመኑ ትውልድ ሰው ነው። ዲያቢሎስም ካቶሊኩን ተጠጋና በሹፈት *"እሺ እንዴት ነው ቃጠሎውን ወደድከው?"* ብሎ የጠይቀዋል። ካቶሊኩም በአፍንጫው እየተነፈሰ "እኔው ራሴ ፈልጌ ያዘዝኩት ነው" ሲል መለሰለት። ዲያቢሎስም በመቀጠል አይሁዱን *"እሺ እንዴት ነው ቃጠሎውን ወደድከው?"* ሲል ይጠይቀዋል። አይሁዱም *"ከዚህ የበለጠ ገሃነም እንጂ ሌላ ምን እጠብቃለሁ"* የዘመኑ ትውልድ ወደ ሆነው ሠውዬ ይጠጋል። የዘመኑ ሠውም *"ቃጠሎ?...የምን ቃጠሎ ነው የምትለው?"* ሲል በላብ እንደተጠመቀ ዲያቢሎስን መልሶ ጠየቀው።

በጣም ጥሩ ቀልድ ነው። የሆነው ሆኖ እኔ *ችግሩን እርሱት* ወይም ደግሞ *ችግሩ ቢኖርም ልክ እንደሌለ አድርጋችሁ አስቡት* እያልኩ አይደለም። የእኔ አባባል ሁኔታውን ልብ ብላችሁ እንድታስተውሉና ስለሁኔታው ያላችሁን ከፍተኛ እውነታ እንድትናገሩ ነው።

*ችስታ ከሆናችሁ ችስታ* ናችሁ። ስለችስታነታችሁ መዋሸት፣ ወይም ችስትነታችሁን ላለመቀበል ስትሉ የሌለ ተረት ተረት መፍጠር ፋይዳ ቢስና ለከፋ ውጤት የሚዳርግ ነው የሚሆነው። ነገር ግን ዋናው ነገር፣ ስለነገሩ ያላችሁ *አስተሳሰብ* ነው። *"ችስታነት መጥፎ ነው"*፣ *"ይህ ዘግናኝ ነው"*፣ *"እኔ ከንቱ ሰው ነኝ ምክንያቱም ጠንክረው የሚሰሩና የሚጥሩ ሰዎች ፈጽሞ ሊቸስቱ አይችሉም"* ወዘተ... የሚሉት ቃላቶች ተናጋሪው *"ስለችስትነት"* ያለውን አመለካከት ወይም አረዳድ የሚያሳዩ ናቸው። ለምን ያህል ጊዜ ችስታ ሆናችሁ እንደምትዘልቁ የሚወስኑት ስለችስትነት የምትናገሩዋቸው "ችስታ ነኝ"፣ "ድንቡሎ እንኳ የለኝም"፣ "ቤሳ በስቴን እንኳ የለኝም" የሚሉት ቃላቶች ናቸው። ከዚህ ጋር በተያያዘ የምታደርጓቸው ድርጊቶች፣ ማለትም *በራሳችሁ ማዘን፣ ገንዘብ ለማግኘት አማራጭ መንገዶችን ከማየት ይልቅ እጅን አጣጥፎ መቀመጥ፣ "ለነገሩ ገንዘብ ምን ጥቅም አለው?" የሚል አመለካከት ማራመዳችሁ* ነው ለረጅም

ቆየኝማ! ዲያቢሎስን መምሰል የሚፈልገው ደግሞ ማን ነው?

እናንተ ናችኋ! "ሁላችሁም ሃጢአተኛ ሆናችሁ ነው የተወለዳችሁት" ብለው የሚያስተምሩ ሃይማኖቶችን ፈጥራችኋል፡፡ ለክፉ ድርጊቶቻችሁ ማስተባበያ ምክንያት ይሆናችሁ ዘንድ "ስትወለዱ ጀምሮ ሃጢአተኞች ናችሁ" ብለው የሚያስተምሩ ሃይማኖቶችን ፈጥራችኋል፡፡ ነገር ግን እኔ "ከአምላክ ተወልዳችኋል" ብዬ ስነግራችሁ፣ "ገና ስትወለዱ ንጹህ አምላክና አማልክት ናችሁ" ስላችሁ አልተቀበላችሁኝም፡፡

ህይወታችሁን በሙሉ ያሳለፋችሁት "መጥፎዎች ነን" ብላችሁ አምናችሁ እንድትቀበሉ ተደርጋችሁ ነው፡፡ "መጥፎ" የተባሉት እናንተ ብቻ ሳትሆኑ የምትሿቸውም ነገሮች ሁሉ ናቸው፡፡ "ወሲብ መጥፎ ነው፣ ብዙ ነገሮችን ማካበት መጥፎ ነው" በጣም ብዙ ነገሮች መጥፎ ናቸው፡፡ እንዲያውም አንዳንድ ሃይማኖቶቻችሁ "ዳንስ መጥፎ ነው፣ ሙዚቃም መጥፎ ነው፣ በሕይወት መደሰት መጥፎ ነው" ብላችሁ እንድታምኑም አድርገዋችኋል፡፡ ቀጥሎ "መሣቅ መጥፎ ነው፣ ፈገግታ መጥፎ ነው፣ ማፍቀር መጥፎ ነው" በሚለውም መስማማታችሁ አይቀርም፡፡ እንደዚያ አይደለም ጓደኞቼ! ብዙ ነገሮች ግልጽ ላይሆኑላችሁ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን አንድ ነገር ለእናንተ ግልጽ ነው፡፡ ይኸውም መጥፎ የተባሉት ነገሮች እናንተ የምታምኑባቸውና የምትፈልጓቸው ነገሮች ናቸው፡፡ ራሳችሁን እንደዚህ ነኝ ብላችሁ ከፈረጃችሁ፣ ቀጣዩ ስራችሁ የተሻለ ለመሆን መጣር መሆኑን ወስናችኋል፡፡ ይህ ምንም ችግር የለውም፡፡ ልብ በሉ፣ በማንኛውም ሁኔታ መድረሻ ግቡ ተመሣሣይ ነው፡፡ ሆኖም በቶሎ የሚያደርስ መንገድ አለ፣ አቋራጭ አለ፣ አፋጣኝ መንገድ አለ ነው ነገሩ፡፡

እሱ ምንድነው?

በአሁኗ ቅጽበት ማንነታችሁንና ምንነታችሁን መቀበልና ያንንም መግለጽ፣ ማሣየት፡፡ እየሱስ ያደረገው ይህንኑ ነው፡፡ የቡድሃ መንገድ ይህ ነው፡፡ የክርሽና መንገድ ይህ ነው፡፡ ምድራችሁን የረገጡ ነብያት ሁሉ መንገዳቸው ይህ ነው፡፡

እያንዳንዱ ነብይም ተመሣሣይ መልእክት ነው ያለው፡፡ የሁሉም መልእክት "እኔ ማለት እናንተ ናችሁ፣ እኔ የማደርገውን ሁሉ እናንተም ማድረግ ትችላላችሁ፣ እነዚህንና ከነዚህም የበለጡ ነገሮችን ታደርጋላችሁ" የሚል ነው፡፡ ነገር ግን አትሰሙም፡፡ ይልቁንም "ዲያቢሎስ ነኝ፣ ክፉው ነኝ" ብሎ የሚሰብከውን የአንዱን አስቸጋሪ መንገድ መርጣችኋል፡፡ "የክርስቶስን መንገድ መከተል አስቸጋሪ ነው"ትላላችሁ፣ "የቡድሃን ትምህርት መከተል፣ የክሪሽናን ብርሃን መጨበጥ፣ ረቢ መሆን አስቸጋሪና ከባድ ነው" ትላላችሁ፡፡ እኔ ግን ይህንን እላችኋለሁ - እጅግ አስቸጋሪው ነገር የራስን

ማንነት መካድ ነው።

እናንተ መልካምነት፣ ምህረት፣ ርሕራሄና መረዳት ናችሁ። እናንተ ሠላም፣ ደስታና ብርሃን ናችሁ። እናንተ ይቅር ባይነት፣ ትሕግስት፣ ጥንካሬና ወኔ ናችሁ። በችግር ጊዜ ረዳት፣ በሃዘን ጊዜ አጽናኝ፣ በጉዳት ጊዜ ፈዋሽ፣ ግራ በመጋባት ጊዜ መምህር ናችሁ። እናንተ ጥልቅ ጥበብ እና እጅግ የላቀው እውነት ናችሁ፣ ታላቅ ሠላም እና የላቀው ፍቅር ናችሁ። በሕይወት ዘመናችሁም እነዚህን ነገሮች እንደሆናችሁ ያወቃችሁበት ጊዜ አለ። እነዚህን ነገሮች መሆናችሁን ለማወቅ ሁልጊዜም መሻት አለባችሁ።

# 4

– ፐ! መንፈሴን ቀሰቀስከው፣ አነቃቃኸኝ!

እምላክ ካላነቃቃችሁ ታዲያ የትኛው ሠይጣን ሊያነቃቃችሁ ነው?

Q1 **በቃ ታሾፋለህ አይደል?**

እንደዚያ ያልኩት ለማሾፍ አይደለም፣ የተናገርኩትን እንደገና አንብቡት።

Q2 **…እሃ ገባኝ**

እዎ፣ ያም ሆኖ ግን ማሾፌ ችግር ያለው አይመስለኝም። አይደለም እንዴ?

Q3 **እኔ እንጃ! እኔ አምላክን እስከዛሬ አስበው የነበረው *ኮስታራ* አይነት እንደሆነ ነው።**

ደህና አንድ ውለታ ዋሉልኝ። እኔን *"እንዲህ ነው"* ብላችሁ አትጠሩኝ፣ አትገድቡኝ። በነገራችን ላይ ለራሣችሁም ይህንን ውለታ ዋሉ።

ቀልድ አዋቂና ጨዋታ ወዳጅ ነኝ። ሕይወታችሁን በሙሉ ምን እንደሠራችሁ መለስ ብላችሁ በተመለከታችሁ ጊዜ፣ የእናንተ ቀልድና ጨዋታ አዋቂነትም በደንብ ይታያል። አይደላችሁም እንዴ? ማለቴ አንዳንድ ጊዜ ነገረ ሥራችሁ ሁሉ ያስቀኛል። ለነገሩ ምንም ችግር የለውም፣ ምክንያቱም በመጨረሻ ሁሉም ነገር እንደሚስተካከል አውቃለሁና።

Q4 **እንደዚህ ስትል ምን ማለትህ ነው?**

በጨዋታው ተሸናፊ አትሆኑም ማለቴ ነው። እንደተሣሣታችሁ አትቀሩም። ምክንያቱም የእቅዱ አካል አይደለምና። ወይም ወደምትጓዙበት ሣትደርሱ አትቀሩም። መዳረሻችሁን የምትስቱበት አንዳችም ምክንያት አይኖርም። ሊሳማችሁ አምላክ ከሆነ እድለኞች ናችሁ። አምላክ እጅግ ግዙፍ በመሆኑ ልትስቱት አትችሉምና።

Q5 **በእርግጥ ስጋታችን እሱ ነው፣ ትልቁ ስጋታችን ምናልባትም "ነገሮች ተመሠቃቅለውብን እስከዘልአለሙ አንተን ሣናገኝ፣ ከአንተ ጋር ሣንሆን እንቀራለን" የሚለው ነው ስጋታችን።**

→ "ገነት ስለመግባት" ነው?

**ያህል ነው ነገሩን ያቀለልከው። ግን ሲናገሯቸው እንጂ ሲያደርጓቸው የሚቀሉ አይደሉም "ጠማማ አስተሳሰቦችን በሙሉ ከአዕምሮህ ማህደር አውጥተህ ጣል" የሚለው ንባዱ ሆድህ ኤሽሪስት ተራራን ውጣ እንደማለት ነው። ከባድ ትዕዛዝ ነው።**

አሳብን መግራትና መቆጣጠር እንደምታስቡት ከባድ አይደለም፣ (ኤቨረስት ተራራን በባዶ ሆድ መውጣትም ቢሆን ከባድ አይደለም) ዋናው ነገር ለሥነ-ስርዓት ተገዥነት ነው። ዋናው የተነሣችሁበት ዓላማ ነው።

የመጀመሪያው ደረጃ አሳቦችን እንዴት በጥንቃቄ መከታተል እንደምትችሉ መማር ነው። ማለትም ስለምን እያሰባችሁ እንደሆነ ማሀብ ማለት ነው። አዕምሯችሁ ጠማማ አሣቦችን ሲያስተናግድና ስለ አንድ ነገር ያላችሁን እጅግ ከፍተኛ የሆነ አስተሳሰብ ሲበርዝ ከያዛችሁት፣ መልሳችሁ እንደገና አስቡ! እንደዚህ እንድታደርጉም እፈልጋለሁ። "ደብሮኛል"፣ "ደስ አላለኝም" ብላችሁ ካሠባችሁ፣ ነገር ግን ከዚህ አሣብ አንዳችም ጥሩ ነገር ካላገኛችሁ እንደገና አስቡ። "ዓለም በጠማማ ክስተቶች የተሞላች መጥፎ ቦታ ናት" የሚል አሳብ ከመጣባችሁ እንደገና አስቡ! ሕይወታችሁ እየወደቀና፣ ተመልሶ ሊሻሻል የማይችል ሆኖ ከታሰባችሁ፣ እንደገና አስቡ።

ይህንን ለማድረግ ራሣችሁን ልታለማምዱ ትችላላችሁ። ባለማድረግ ምን ያህል ራሣችሁን በደንብ እንዳሰለጠናችሁ መለስ ብላችሁ መመልከት ነው።

**አመሰግናለሁ። እንደዚህ ጥርት ያለ፣ የተብራራ የአሰራር ሂደት አጋጥሞኝ አያውቅም። ሲናገሯቸው እንደሚቀሉት ሁሉ ለማድረግም የቀለሉ ይሆኑልን ዘንድ እመኛለሁ። አሁን በእርግጥ ቀልጭ ባለ መልኩ የተብራራልኝ ይመስለኛል።**

መልካም፣ ወደ ኋላ መለስ ብለህ መከለስ ካስፈለገህ፣ በዋቢነት የሚያገለግሉ ብዙ የህይወት ዘመናት ስላሉን ችግር የለውም፣ ዞር ብለህ መከለስ ትችላለህ።

የደማነት ጉዳይ ነው የሚሆነው፣ እዚያ መቼ ይደረሣል የሚል ጥያቄ ብቻ፡፡ ይህም ቢሆን የማይጨበጥ ነገር ነው፡፡ ምክንያቱም መቼ የሚለውንም ሆነ በፊትና በኋላ የሚሉትን ጉዳዮች ማገናኘት አይቻልምና፡፡ ያለው ራሳችሁን የምታውቁበት ዘለዓለማዊና ሁለንተናዊ የሆነው ·አሁን· ብቻ ነው፡፡

> ታዲያ ነጥቡ ከምን ላይ ነው? እዚያ ካለመድረስ መንገድ ካለ የህይወት ቁም ነገሩ ምንድነው? ስለምናደርገው ነገር ሁሉ መጨነቃችን ስለምን አስፈለገ?

በእርግጥ መጨነቅ የለባችሁም፡፡ ግን ጥሩ ተመልካች ለመሆን በደንብ መስራት አለባችሁ፡፡ በቀላሉ ምን እንደሆናችሁ፣ ምን እንደምታደርጉና ምን እንዳላችሁ መመልከት፣ ይህም ለእናንተ ምን ጠቀሜታ እንዳለው ማጤን ብቻ ነው፡፡

የህይወት ቁምነገሩ አንድ ቦታ መድረስ አይደለም፡፡ በፊትም ሆነ አሁን ልትደርሱበት በምትፈልጉት ቦታ ላይ እንደሆናችሁ ማስተዋል ብቻ ነው የሚጠበቅባችሁ፡፡ ሁሌም ዘልአለማዊ በሆነ የፈጠራ ሂደት ውስጥ ነው ያላችሁት፡፡ ስለዚህ የህይወት ቁም ነገሩ መፍጠር ነው፡፡ ማንና ምን እንደሆናችሁ ማወቅና መረዳት ነው፡፡

ይህንን ጥያቄ ቀድሞ ቢሉ አንስታችሁታል፤ መልሱ ያው ነው። ምን ልዩነት አለው፤ ምናልባት እኔ የምናገረውን ሁሉ ስህተት ነው ካላችሁ ስለ የተሻለ የህይወት መንገድ ሊያሳዩኝ ትችላላችሁ?

የለም።

እንግዲያውስ "ስህተት" ትክክል ነው፤ "ትክክል" ደግሞ ስህተት ነው ማለት ነው!

ከመላወል ስሜት መውጣት እንድትችሉ በድጋሚ ይህንን እነግራችኋለሁ። የተናገርኩትን አንዱንም ነገር አትመኑ፤ በህይወታችሁ ተግብሩት፤ ኑሩበት እንጂ። ከዚያ ከፈለጋችሁ የራሳችሁን የተለየ የህይወት መመሪያ ፈጥራችሁ ኑሩ። ይህ እንዳለ ሆኖ የራሳችሁን እውነት ለማግኘት የህይወት ገጠመኞቻችሁን ተመልከቱ።

ትልቅ ወኔ ካላችሁ አንድ ቀን ፍቅር መፍጠር ጦርነት ከመፍጠር የተሻለ መሆኑ የተረጋገጠበትን ዓለም ታያላችሁ። በዚያም ቀን ሃሴትን ታደርጋላችሁ።

# 9

"በእውነተኛ ማንነታችሁ ሁኑ፤ ራሳችሁን ሁኑ" የሚለው ቀላል ነገር መስሎ ሊታያችሁ ይችላል። ነገር ግን በህይወታችሁ ከምታከናውኗቸው ነገሮች እጅግ ፈታኙ ነገር ይህ ነው። በእውነት ለመናገር እዚህ ደረጃ ላይ ላትደርሱም ትችላላችሁ። ለዚህ የሚበቁት ጥቂት ሠዎች ናቸው። በአንድ ወይም በብዙ የህይወት ዘመንም አይሆንም።

> ታዲያ መሞከሩ ለምን አስፈለገ? በቀላሉ "እንዲሁ እንዳለኸው ህይወትን ኑር" ማለቱ አይሻልም? "ግሃነም የለም፤ ቅጣት የለም፤ የምታጣው ነገር የለም" ብለሃል። ታዲያ ምን ለማሸነፍ ወይም ለማግኘት ነው መልፋቱ? እዚያ ደረጃ ላይ ለመድረስ አስቸጋሪ ነው ማለትህ እንዳለ ሆኖ፤ እዚያ ደረጃ ላይ ለመድረስ የምናደርገው ጥረት ምንድነው የሚያተርፍልን? ይህ የአምላክና ራስን የመሆን ጉዳይ ማያጨናንቀን ባለን የህይወት ዘመን ዘና ብለን አንኖርም?

የኔ ልጅ፣ ሰግተናል። አልሰጋንም እንጂ ...

> አንተ እዚህ መጥተህ እንድትነግረኝ አስሬ የምለፋው፣ በቃ ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ፣ የሚሳካለትም ከሚሊዮን አንዱ ብቻ እንደሆነ እንድትነግረኝ ነው ማለት ነው።

እንዳለፋሁህ አውቃለሁ። ምን ልረዳህ እንደምችል እስቲ ልያለሁ። "*በዚህ ምክንያት ጊዜዬን አባክኛለሁ*" ያልከውን ነቅሼ ልውሰድ። ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ይህ የመጀመሪያ ሙከራህ ይመስልሃል?

> ምንም የማውቀው ነገር የለም።

ከዚህ በፊት እዚህ የነበርክ አይመስልም?

> እንዳንዴ።

ግን ብዙ ጊዜ ነበርክ።

> ስንት ጊዜ?

ብዙ ጊዜ።

> እኔን ለማበረታታት ብለህ ነው?

አንተን ለማነቃቃት ነው።

> እኮ እንዴት?

በመጀመሪያ ጭንቀትን ያስወጣል። ከዚያም እናንተ የምትሉትን የ"*ይቻላል*"

ይልቁንም በእምላክ መዛበት ነው።

## ስለዚህ ከመግደል ጋር በተያያዘ ስህተት እለ ማለት ነው?

እስቲ እናጠናክረው። *ስህተት* የሚባል ነገር የለም። *ስህተት* እንግራዊና እናንተ *ትክክል* ብላችሁ ለምትጠሩት ነገር ተቃራኒ መግለጫ ነው። ያም ሆኖ *ትክክል* ምንድነው? በዚህ ጉዳይ ላይ ሣትወገኑ ገለልተኛ አቋም ይዛችሁ መናገር ትችላላችሁ? ነው ወይስ *ትክክል*ና *ስህተት* የሚሉት ቃላቶች በምታሣልፏቸው ገጠመኞች ወይም በሚያጋጥሟችሁ ክስተቶች ላይ እናንተ የምትሠጡትን ውሣኔ ለመግለጽ የምትጠቀሙባቸው ቃላቶች ናቸው? ውሣኔዎቻችሁ የተመሠረቱትስ በምን ላይ ነው? እስቲ ንገሩኝ? ውሳኔዎቻችሁ የራሳችሁ ኑረት ወይም ልምድ? አይደሉምን?

አብዛኛውን ጊዜ የምትፈልጉት የራሳችሁን ሳይሆን *የሌላውን ውሣኔ መቀበልን* ነው። ከእናንተ በፊት የመጣውን ወይም ከእኛ የተሻለ እውቀት አለው ብላችሁ የምታስቡትን ሠው ውሣኔ ነው የምትቀበሉት። በራሳችሁ እውቀት ላይ ተመርኩዛችሁ *ትክክል* ነው ወይም *የተሣሣተ* ነው በሚል የወሠናችሁት ነገር ቢኖር እጅግ ጥቂት ነው።

ይህ በተለይም ወሣኝ በሆኑ ጉዳዮች በጉልህ የሚስተዋል ነው። በእርግጥ በጣም ወሳኝ የሆነ ጉዳይ ባጋጠመን ቁጥር የራሣችንን ተሞክሮና ልምድ ከማዳመጥ ይልቅ የሌላ ሠውን አሣብ ወደመቀበሉ ነው የምናዘነብለው። ይህም በራሱ *በራሣችሁ ህይወት ውስጥ ያሉ ወሣኝ ሁኔታዎችን መቆጣጠር የምታቆሙበትን፣ በሰብዓዊ ህይወት ውስጥ የሚነሱ ጥያቄዎችን ወደ ጎን የምትተዉበትን ምክንያት የሚያሳይ ነው።*

ይህ ጉዳይ ለነፍሣችሁ ወሣኝ የሆኑ ርዕሰ ጉዳዮችንም የሚያካትት ነው– የእምላክ ምንነትን፣ የእውነተኛ ስነ ምግባር ባህርይን፣ የእውነት ጥያቄን፣ በጦርነት መሃል ያለ የህይወትና የሞት ጉዳይን፣ ህክምናን፣ ውርጃን አጠቃላይ የግል እሴቶችን፣ መዋቅርን፣ ፍረጃን ወይም ድምዳሜን ሁሉ ያካትታል። አብዛኞቻችሁ ይህንን ከራሳችሁ አሳልፋችሁ ለሌሎች ሠዎች አስተላልፋችኋል። በእነዚህ ጉዳዮች የራሳችሁን ውሣኔ መስጠት አታውቁም፣ አትፈልጉም።

በነገራችን ላይ ሃይማኖቶች የተስፋፉትም በዚህ ምክንያት ነው። እንዲሆንላቸው በሚጠብቁት አንጻር ምዕመናኑ ጠንካራ፣ የማይለዋወጥ እና ግትር እስከሆነ ድረስ ስለእምነቱ ቀኖና ደንታ የላቸውም። በጣም እንግዳ የሆነ ነገር እና እምነት በእምላክ ስም ይስተናገዳል። *“ይህ የእምላክ መንገድ፣ የእምላክ ቃል ነው”* ይላሉ። ይህንንም በደስታ የሚቀበሉ ሰዎች አሉ፣ ምክንያቱም እንደዚህ አይነቱ እምነት *የማሰብን አስፈላጊነት*

ማለት ያለብኝ ይመስለኛል።

ስለዚህ ልጆቼ አድገታችሁን ቀጥሉ፡፡ መሆናችሁን ቀጥሉ፡፡ በከፍተኛው የማንነት ትርጉም ምን ለመሆን እንደምትፈልጉ መወሰንን ቀጥሉ፡፡ እዚያ ለመድረስ ሥራችሁን ቀጥሉ፡፡ ቀጥሉ! ቀጥሉ! ይህ የአምላክ ሥራ ነው፡፡ ለዚህም ነው እናንተና እኔ ያለነው፡፡ ስለዚህ ቀጥሉ!

# 10

Only in ONE Chapter! LOVE

**1** እወድሃለሁ፡፡ ያንን ታውቃለህ?

እንደምትወዱኝ አውቃለሁ፡፡ እኔም እወዳችኋለሁ፡፡

# 12

**በህይወቴ መስራት የምፈልገውን ነገር በመስራት ለመተዳደሪያዬ የሚሆን ነገር ማመቻቸት ያልቻልኩት ለምንድነው?**

*ምን? በሕይወቴ እንደፈለኩት በደስታ እየኖርኩ ለምን ተቀማጭ ደግሞ አይኖረኝም ነው የምትለው? ወንድሜ እያለምክ ነው?*

**ምን?**

ስቀልድ ነው! እንዲሁ ትንሽ አዕምሮህን ለማንበብ ያህል ነው:: አየህ፣ ስለዚህ ነገር የአንተ አስተሣሠብ እንደዚህ ነበር::

**የእኔ የህይወት ተሞክሮ ነበር::**

እም:: በዚህ ጉዳይ ላይ ብዙ ተነጋግረናል:: የሚወዱትን ስራ በመስራት ኑሮአቸውን የመሠረቱ ሠዎች በዚያው ሥራቸው ገፍተው የሚቀጥሉ ሰዎች ናቸው:: እጅ አይሠጡም፣ አይሸነፉም:: የሚወዱትን ሥራ ለመስራት ሲሉ ህይወትን ይጋፈጣሉ::

ነገር ግን በህይወት ሥራ ሌላ መነሣት ያለበት፣ በብዙ ሠዎች ዘንድ የጎደለ አንድ ነገር አለ::

**ምንድነው እሱ?**

በመሆንና በማድረግ መካከል ልዩነት አለ:: ብዙ ሠዎች ግን ትኩረት የሚሠጡት ማድረግ ለሚለው ነው::

**እና እንደዚያ ማድረግ አልነበረባቸውም?**

*"አለባቸው" ወይም "የለባቸውም" የሚል ቃል እዚህ መግባት የለበትም:: ያለው የምትመርጡት ነገር እና የመረጣችሁትን እንዴት ልታገኙት ትችላላችሁ የሚለው ነገር ብቻ ነው:: ሠላምን፣ ደስታንና ፍቅርን ብትመርጡ፣ በምትሰሩት ሥራ (በማድረግ) የምትፈልጉትን ያህል ልታገኟቸው አትችሉም:: ደስታና እርካታን የምትፈልጉ ከሆነ እነዚህንም በጥቂቱ ነው በሥራ (በማድረግ) የምታገኟቸው:: ከእምላክ ጋር አንድ የተሟላ ግንዛቤን፣ ፍፁም እውቀትን፣ ጥልቅ መረዳትን፣ የማያልቅ ርህራሄን፣ ፍፁም የሆነ ስኬትን የምትፈልጉ ከሆነ፣ እነዚህን በሥራ (በማድረግ) ልታሟሉ አትችሉም::*

ባላችሁ ነገር ትጥራላችሁ።

[ የምትፈልገውን ነገር ማግኘት አልችልም፣

አይቻልም።

ቀደም ብለህ፣ ይህንን ቃለ ምልልስ ስንጀምር እንዳልከው ይህንን ለማወቅ እስካሁን ድረስ ሲገባኝ አልቻለም። የፈለኩትን ነገር ሁሉ ማግኘት እንደምችል የነገርከኝም ይመስለኛል - እንደ ለላዕቡና እንደ እምነትህ ይደረግልሃል አይነት ነገር።

ሁለቱ አባባሎች እርስ በርሣቸው የሚጣረሱ አይደሉም።

ለእኔ ግን በእርግጠኝነት የሚጣረሱ ሆነው ነው የታዩኝ።

ያ የሆነው የመረዳት ብቃት ስለሚጎድልህ ነው።

ደህና፣ አሁን ያልከውን እቀበላለሁ። ለዚህም ነው ከአንተ ጋር የማወጋው።

እንግዲያውስ ላብራራው። የምትፈልጉትን ማንኛውም ነገር ሊኖራችሁ አይችልም። ቀደም ሲል በምዕራፍ አንድ ላይ እንደተናገርኩት፣ አንድን ነገር ለማግኘት የሚደረግ ጥረት በተቃራኒው ያንን የሚፈለገውን ነገር እንዳይመጣ ገፍቶ ያስቀረዋል።

ደህና፣ ቀደም ሲል ተናግረኸው ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ሣልጨብጠው እያመለጠኝ ነበር።

አብሮ ለመጓዝ ታገል። አሁንም ጠለቅ ባለ መልኩ እቀጥልበታለሁ። በደንብ ተከታተሉኝ። ወደ ተረዳችሁት ጉዳይ እንመለስ - አሣብ ፈጣሪ ነው። ተግባባን?

አዎ።

ቃል ፈጣሪ ነው። ይህንንም አውቃችኋል?

አውቀያለሁ።

ድርጊት ፈጣሪ ነው። አሣብ፣ ቃል እና ድርጊት እነዚህ ሦስቱ የፈጠራ ደረጃዎች ናቸው። አሁንም ከእኔ ጋር ናችሁ?

አዎ ካንተ ጋር ነኝ።

መልካም። አሁን ዓለማዊ ስኬት የሚለውን ነገር ርዕሰ ጉዳያችን አድርገን እንውሰድ። ከቅድም ጀምሮ እያወራችሁትና እየጠየቃችሁት ያለው ጉዳይ እሱ ነውና።

ወቅ ጉድ።

ይህ ከሆነ ዘንዳ ቢያንስ ደስታዬን ነጥቀውኛል ብላችሁ በምታስቧቸው ሠዎች ከመበሳጨትና ከመነቀፍ ትገላገላላችሁ።

በሥጋ የምትሠሩት ሥራ ፋይዳ የለውም አይባልም። በጣም ጠቃሚ ነው። ግን እናንተ በምታስቡት መልኩ አይደለም። በሥጋ የምትሠሩት ሥራ የማንነታችሁ መገለጫ /ነፀብራቅ/ ነው እንጂ ማንነታችሁን ለማወቅ የሚደረግ ጥረት አይደለም።

በነገሮች እውነተኛ ቅደም ተከተል አንድ ሠው አንድ ነገር የሚሠራው ደስተኛ ለመሆን አይደለም። አንድ ሠው አንድ ነገር እስከሠራ ድረስ ደስተኛ ነው። ሩህሩህ ለመሆን አንድ ሠው አንድ ነገር አይሠራም። ሩህሩህ ስለሆነ ሥራውም እንደዚያው ነው። በከፍተኛ የንቃተ ህሊና ደረጃ ላይ ባለ ሠው ዘንድ የነፍስ ውሣኔ የሥጋ ተግባርን ተከትሎ የሚመጣ ነው። *በደመነፍስ የሚንቀሣቀስ ሠው* ብቻ ነው በሥጋው ድርጊት ከላቀ የነፍስ ደረጃ ላይ እደርሣለሁ ብሎ የሚያስበው። "*ህይወትህ ሥጋህ* የሚሠራው ሥራ አይደለም" የሚባለውም ለዚህ ነው። ይህ እንዳለ ሆኖ በሥጋችሁ የምትሠሩት ሥራ የህይወታችሁ ገጽታ ነጸብራቅ መሆኑም እውነት ነው።

ይህም ሌላ መለከኮታዊ ጣምራ በቆልት ነው። ቢሆንም ሌላ መገንዘብ የምትፈልጉት ነገር ከሌለ ይህንን እወቁ። ልጅ ኖራችሁም አልኖራችሁ፣ ትዳር ኖራችሁም አልኖራችሁ ደስታችሁን የማጣጣም መብት አላችሁ። ፈልጉት! አግኙት! ብዙ ገንዘብ አገኛችሁም አላገኛችሁ ደስተኛ ቤተሠብ ይኖራችኋል። የቤተሰባችሁ አባላት ደስተኛ ካልሆኑና ተነስተው ጥሎዋችሁ ቢሄዱ የራሣቸውን ደስታ ያገኙ ዘንድ በፍቅር ሸኟቸው። በሌላ በኩል የሥጋ ነገር ከማያሣስባችሁ ደረጃ ላይ የደረሳችሁ ሠዎች ከሆናችሁ ደስታችሁን ለማግኘት ነፃ ትሆናላችሁ - በሠማይ እንደሆነው ሁሉ በምድርም። አምላክ *መደሠት መልካም ነው* ይላል - አ በሥራችሁም ጭምር ደስተኛ መሆን።

የህይወታችሁ ሥራ *እኔ ማን ነኝ* የሚለው አረፍተ ነገር ነው። ምንም ነገር መስራት የለባችሁም። ቤተሰቡን የሚረዳና በተቻለው አቅም ደስታውንም ሁሉ የሚወድ አይነት ሠው ከሆናችሁ ሥራችሁንም ውደዱ። ምክንያቱም ስለ እናንተ ህያው የሆነ አረፍተ ነገር ለመፍጠር ሁኔታዎችን ያመቻቻ ነውና። አንቺ ሃላፊነትን ለመወጣት ስትይ በምትጠይው ሥራ የተሠማራሽ ሠው ከሆንሽ ሥራሽን ውደጂ፣ ምክንያቱም ሙሉ ለሙሉ የራስሽን ሥዕል የራስሽን አስተሣሠብ ይደግፋልና።

*ማንም ሠው የሚሠራውን ሥራ ካወቀና ለምን እንደሚሠራው ከተረዳ* ሁሉንም ነገር መውደዱ አይቀርም። ማንም ሰው መስራት የማይፈልገውን ነገር አይሠራም።

# 13

**ያጋጠሙኝን የጤና እክሎች እንዴት ነው መፍታት የምችለው? ላለፉት ሦስት የህይወት ዘመናት ሥር የሰደደ ደዌ ሠለባ ነበርኩ። ለምንድነው አሁን በዚህ የህይወት ዘመኔ እነዚህ ችግሮች እንደገና የደረሱብኝ?**

በመጀመሪያ ቀጥታ አንድ ነገር እንበል:: አብዛኞቹን ትወዳቸዋለህ። በሚያስደንቅ ሁኔታ ለራስህ ለማዘን ስትልና ለራስህም ትኩረትን ለማግኘት ስትል በሽታዎቹ እንዲይዙህ ትሻለህ። ምናልባት የምትጠላቸው እየከፉ ሲመጡብህ ብቻ ነው:: መጀመሪያ ስትፈጥራቸው ለስበህ ከነበረው አልፈው እየከፉ ሲመጡ ብቻ ነው የምትጠላቸው::

አሁን ምናልባት ቀደም ሲል የምታውቁትን ነገር በደንብ እናጢነው። ሁሉም በሽታዎች በራስ የሚፈጠሩ ናቸው:: ሌላው ቀርቶ መደበኛ የህክምና ዶክተሮች እንኳ ሳይቀሩ ሠዎች ራሳቸውን እንደሚያሳምሙ እየተገነዘቡ ነው:: ብዙ ሠዎች ሳያውቁት በደመነፍስ ነው ይህንን የሚያደርጉት /ሌላው ቀርቶ ምን እየሠሩ እንደሆነ እንኳ አያውቁም/ ውጫዊ የሆነ ነገር ያመጣባቸው እንጂ ራሳቸው በራሳቸው ላይ ያመጡት አይመስላቸውም።

የሠዎች ህይወት የሚያልፈው ከጤና ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ሳይሆን ከደመነፍሳዊ እንቅስቃሴያቸው ጋር በተያያዘ ጉዳይ ነው::

ሠዎች እያጨሱ ለምን ካንሠር ያዘኝ ብለው ይደነቃሉ። ሥጋ እና ቅባት እየበሉ የደም ግፊት ለምን አጋጠመኝ ብለው ይደናገጣሉ። ህይወታቸውን በሙሉ እየተበሳጩ ለምን የልብ ውጋት ያዘኝ ብለው ያጉረመርማሉ። ከሌሎች ሰዎች ጋር በከፍተኛ የሥራ ጫና ውስጥ ያለ ርህራሄ እየተፎካከሩ ለምን የልብ ድካም አመመኝ ይላሉ:: ያልተለመደው እውነታ ግን ሠዎች

13

ያጋጠሙኝን የጤና እክሎች እንዴት ነው መፍታት የምችለው? ላለፉት ሦስት የህይወት ዘመናት ሥር የሰደደ ደዌ ሠለባ ነበርኩ።

አሁን በጨረፍታ ያያችሁት እውነታ በፍፁም የማያልቅ መሆኑን ብነግራችሁ ምን ታደርጋላችሁ?

እስቲ ይህንን ግልጽ አድርገው። ግልጽ እንድታደርገልኝ እጠይቅሃለሁ።

ቅንጣት ነው ብላችሁ የምትገምቱትን የጎዋ አካል ውሰዱ። ይህንን የቅንጣት ቅንጣት የሆነ ብናኝ ቁስ እስቲ አስቡት።

እሺ።

አሁን ያን ቅንጣት ከሁለት ክፈሉት።

እሺ።

ምን አገኛችሁ?

ሁለት በጣም ያነሱ ክፍልፋዮች።

ትክክል። አሁንም እንደገና፣ ደግማችሁ ደጋግማችሁ ከፋፍሉት። ምን ቀረ?

የቅንጣት ቅንጣት የሆኑ ብናኞች።

እ። ግን ማቆሚያው መቼ ነው? ቁስ አካልን ምን ያህል ጊዜ ብትትከፋፍሉት ነው የሚጠፋው?

አላውቅም። ግን ፈጽሞ እንደማይጠፋ እገምታለሁ።

ሙሉ በሙሉ ሳጠፋው ፈጽሞ አልችልም፣ ትርጹን ከመለወጥ በስተቀር ማለትህ ነው?

እንደዚያ ማለት ይመስለኛል።

ይህንን አላችኋለሁ - የህይወትን ሁሉ ምስጢር ተምራችኋል። በዚህም አዕላፍን (infinity) ተመልክታችኋል። አሁን የምጠይቃችሁ ጥያቄ አለኝ።

እሺ ...

አዕላፍ ወደ አገር አቅጣጫ ነው የሚሄደው ብላችሁ እንድታስቡ ያደረጋችሁ ምንድነው?

ወደላይ ማብቂያ ከሌለው ወደታችም ማብቂያ አይኖረውም ማለት ነው።

ላይም ሆነ ታች የሚባል ነገር የለም ግን ማለት የፈለግኸው ገብቶኛል።

እንደዚሁም ሁሉ እናንተ በሌድጋት ሂደት ውስጥ ናችሁ ወይም ደግሞ ሀሳብ መቋቋም በተደጋጋሚ እንዳስቀመጥኩት በመሆን ሂደት ውስጥ ናችሁ።

በኑሯችሁ ላይ ምንም ገደብ የለውም።

ድፍረት አይሆንብኝና አምላክ መሆንም ችሎታችሁ ነው የምትለኝ ልክ እንዳንተ?

ምን ይመስላችኋል?

አላውቅም።

ይህንን እስከታውቁ ድረስ ልትሆኑ አትችሉም። ሦስቱ ማዕዘኑን አስታውሱ፣ ቅድስት ስላሴን፣ መንፈስ - አዕምሮ - ሥጋን አስቡ፣ ፍጡሩን አውቃችሁ ኑሩበት። የራሳችሁን ወካይ ቃላት አስታውሱ-

ቅዱስ መንፈስ = መነቃቃት = መጸነስ

አባት = እንክብካቤ = መፍጠር

ልጅ = ዝርያ = ኑረት

ልጅ - በመንፈስ ቅዱስ የተፀነሠውን እንክብካቤ የተባለ አባብ በኑረት ያውቃል። አንድ ቀን ራሳችሁን አምላክ ሆኖ እስባችሁት ታውቃላችሁ?

ነካ በሚያደርገኝ ጊዜያት

ጥሩ፣ ይህንን እላችኋለሁ - እናንተ አምላክ ናችሁ። ችግሩ ያንን አለማወቃችሁ ነው። ካሁን በፊት እናንተ አማልዕክት ናችሁ አላልኳችሁምን?

